# ኢሕአፓ ስለ ጸያፍ ዝልፍያው ይቅርታ መጠየቅ አለበት!

## ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay)

*መግቢያ*

ይህ ሐተታ ለኢሕአፓ መልስ ነው። ይህ ለመጻፍ ስዘጋጅ፤ ከብዙ ጠላቶቹ ጋር ስከላከልለት የነበረው ኢሕአፓ ድንገት ድርጅታዊ ሐተታው እኔንም ሆነ ሌሎች ሰዎች {ስማችን ባይጠቅስም} ፤ "የጉምዝ ሕዝብ ሰድባችኋልና ይቅርታ ጠይቁ" ብሎ ስለጻፈው፤ መልስ ለመስጠት ስዘጋጅ፤ እልክ ውስጥ ገብተን ፖለቲካዊ፤ብሔራዊ፤ሰብአዊና ባሕላዊ ነክ ጉዳዮችን በማጣቀስ ከድርጅቱ ጋር ለመከራከር ነበር በቁጣ ተነስቼ የነበረው።

ሆኖም አሁን ከመጀመሪያው ቁጣዬ የቀነስኩ ስለመሰለኝ ሰከን ብዬ መልስ ለመጻፍ ወሰንኩኝ።ድርጅቱ እንዲህ መሳይ አታካራ ገብቶ ባልጠበቅኩት ዱብ ዕዳ ገብቶ እኔን እና ሞረሽ ወገኔ ተባለው ለአማራ የቆመ ብቸኛ ድርጀትን ሲዘልፈን እጅግ ነበር የበገንኩት። ትልቅ መቆጫ የሚያክል ዱጅነም {ተምዘግዛጊ የፖለቲካ ሚሳይል/አለሎ} ለማዘጋጀት አስቤ ነበር። ሆኖም ድርጅቱን ለቀው የሄዱና አንዳንድ የድርጅቱ አባሎች ያልሆኑ የቅርብ ወዳጆቼ ስለ ሁኔታው መብገኔን አማክሬአቸው ስለነበር፡ እነሱም መበሳጨቴን ተረድተው፤ "ቻል በለውና ቀለል ያለ ትችት ጣልላቸው" ብለው ወገናዊ ምክር ስለለገሱኝ፤ በዚህ ቀለል ባለ ትችት ለመቀጠል ይኼው ኢሕአፓ ስለ ጻፍነው የአማራ ሕብረተሰብ ዜና፤ችግርና እሮሮ "ብልግና ነው" ብሎ በድርጅቱ ስም ለወጣው መግለጫ መልስ፡ ይኼው።

ኢሕአፓ **“ከፍኖተ ዲሞክራሲ፡=  በአማራ ሕዝብ ስም ሌሎችን መዝለፍ የሚወገዝ ነው”** በሚል የድረጅቱ ሐተታ በተነተነው ጽሑፉ ውስጥ በርካታ ነገሮችን ጽፏል።

‘አማራ በጉሙዞች ተገድሎ ስጋው አልተበላም፤ በአገራችንም እንዲህ ያለ ነገር ተከስቶ አያውቅም፤ አፍሪቃን ለሚጠሉ ለፈረንጆች ማስደሰቻ የተዋሸ የውሸት ዜና ነው..... ወዘተ ወዘተ ወዘተ.. ብሎ ዜናውን ስለማጣጣሉ፤ ለዚህም ውሽታሞች ናቸው ብሎ የዓይን ምስክሮችም ጭምሮ በውሸታሞችነት በመዝለፉ፤ ድርጅቱ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል እላለሁ። ሆኖም እንደ ባሕላችን የጨዋ ባሕሪ ተከትለው ይቅርታ ይጠይቃል የሚል እምነት ሕልምም የለኝም።

የድርጁ አንዳንድ መሪዎች ወንድማዊ ወዳጅነት ስላለኝ፤ ክርክራችን ፖለቲካዊ እንጂ የግል ጸብ እንዳልሆነ ላሰምርበት እፈልጋለሁ። አሁንም ወዳጅነታችን እንደሚቀጥል ተስፋ አለኝ። ስንከራከር የመጀመሪያችን ስላልሆነ ፖለቲካ ነውና በዚህ አመለከተዋለሁ።

እንዲህ ነው። ታስታውሱ እንደሆነ፣ ባለፈው ሰሞን በቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ‘ዞን’ በሚኖሩ ዐማሮች ላይ የተፈፀመ የዘር ማጥፋት ወንጀል ካርታ፡- የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ወረዳዎች በዐማሮች ላይ የተፈፀመ ሰብዓዊ መብት ጥሰት ‘ልዩ ዘገባ’ ቅፅ ፫፣ቁጥር ፩ ማክሰኞ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም. ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት[http://moreshinfo.com/archives/2128](http://moreshinfo.com/archives/2128)

በሚል ከሞረሽ ወገኔ ድርጅት የወጣ መግለጫ አንባብችሁ ይሆናል፤ የሚል እምነት አለኝ።

ሐቀኛና ሃላፊነታቸው የሚያውቁ፤አገር ወዳድ እውነተኛ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች የሚያዘጋጁት ሆላንድ ‘ስቶክሆልም’ ከተማ ውስጥ የሚገኝ

'የኢትዮጵያ ራዲዮ ጣቢያም' የሞረሽን መግለጫ በመንተራስ ማጠናከሪያ ይሆን ዘንድ ለናሙና እንዲሆን ተብሎ አጭር ጥያቄና መልስ ከተባረሩት አማራዎች አጭር የቃለ መጠይቅ ቆይታ ያደረገበትን የእማኞች ምስክር ጭምር አድምጣችሁ ይሆናል።

ራዲዮ ጣቢያውም፤ ሆነ ሞረሽ ከቀረበው ማስረጃ በበለጠ ለከሳሾቻችን ግልጽ እንዲሆንላቸው፤ የቀረቡትን ምስክሮች "የአማራ ሰው በጉሙዞች ተገድሎ ስጋው ተበልቷል" የሚለውን፤እነሱም ሆኑ ሌሎችም እማኞችም ካሉ ጭምር ለጥልቅ ቃለ መጠይቅ ብተጋብዟቸው፤ የከሳሾቻችን ጀሮ አንደገና ሊረዳ ይችላል እና ፤በዚህ አዘጋጇዎቹ አስቡበት እላለሁ። ኢሕአፓዎች የተጠራጠሩ ብቻ ሳይሆን "አልተደረግም" የሚል ነው አቋማቸው።

ኢሕአፓ ሞረሽ ወይንም ራዲዮ ጣቢያው አዘጋጆች ያቀረቡት ዜና፤ 'የፈጠራ፤ ልብ ወለድ ዜና እና በመልክአ ምድር መረጃዎች ተደግፎ፤ ተገደሉ፤ተበሉ የተበሉ የሰዎች ስም ዝርዝር ከሰማይ ተፈልስፎ የተሰራጨ ዜና ነው" ብሎ የሚል ወያኔ ብቻ ነው። ኢሕአፓ የወያኔንት ክሕደት ዓይነቱ ቅዠቱን አቁሞ "ፕሮፌሰር አስራትን' አማራን ከጥቃት ለመከላከል ሲጥሩ "የወያኔ የኀሳ አደረጃጀት ድርጊት እየተከተሉ ነው" ብሎ ተደጋጋሚ በአማራ ኀሰኛነት ውንጀላ ሲወነጅላቸው እንደነበረው ሁሉ፤ ሞረሽ ላይም ሆነ የአማራን እሮሮረ ለማስተጋባት በምንጥር ዜኖች ላይ ሹል ብዕሩን የማነጣጠሩን ጉዳይ አንዲቆጥብ ወገናዊ ምክሬን እለግሳለሁ።ባይሆን ይተባበረን።

ኢሕአፓ ጉምዝ ውስጥ አማራዎች በጉሙዞች ታርደው ስጋቸው አልተበላም፤ ኢትዮጵያ ውስጥም የትም ተደርጎ አይታወቅም/ ካሁን በፊትም በባሕላችን አልታየም.....የሚል ኢሕአፓ አለኝ የሚለው የማፍረሻ መረጃው በማቅረብ መረጃው ማሳየት ይጠበቅበታል።

ሞረሽ “የጉሙዝ ጎሳ የአማራን ነገድ ገድሎ በላ” ብሎ በማለቱ “የህችን ሐረግ” መዝዞ “የጉሙዝ ሕዝብ የሰው ስጋ ይበላል ብሎ የጉምዘን ሕዝብን መልካም ስም አጥፍቷል” ፤ ብሎ ሞረሽን ወንጅሏል። ለዚህም “ለጉሙዝ ሕዝብ ይቀርታ ይጠይቅ” ሲል ኢሕአፓ ሞረሽ ላይም ሆነ በተቀረነው የዜናው አሰራጪዎች፤ በደርህቱም ሆነ በጉምዝ ሕዝብ ስም ድርጅቱ ከስሶናል። ኢሕአፓ እየዘላበደው ያለው አጉል እወደድ ባይነት፤ “ይህ ለአማራ የቆመን ሞረሽ የተባለው ብቸኛ ድርጅት ለማፍረስ የታቀደ ሜላ ካልሆነ በስተቀር፤ ኢሕአፓ እውነት ከልቡ አምኖበት ሞረሽ “አማራ ሃይማኖተኛ ነው፤ የጉሙዝ ሕዝብ ‘አረመኔ ሰው በላ’ ነው እና የሰው ስጋ ይበላል” ብሎ፤ ያልተባለውን “ተባለ” እያለ- ድርጅቱንም ሆነ በዜናው የተረባረብን ግለሰቦች ሁሉ እኛን “ትምክሕተኛ፤ ኋላ ቀር፤ ባለጌ...” እያለ መወንጀሉ ኢሕአፓ እንዲህ ያለ ውንጀላ ምንጩ ከየት አንዳገኘው ማሳየት አለበት።

በነገራችን ላይ ከዚህ/ከታች የሚታየው ርዕስ የኔን ጽሑፍ ለማንበብና ኢሕአፓ በድረገጹ በአሲምባ ላይ ተለጥፎ፤ አንድ ቀን ከቆዬ በኋላ እንዳይለጠፍ ያስነሳው ጸሁፌን በኢትዮፓትርዮትስ እና በወልቃይት ድረገጽ፤ወይንም እኔ ባላየኋቸው በተለጠፉ ድረ ገጾች ላይ ስለተለጠፈ ያንን ማንበብ ትችላላችሁ።

በጹሑፌ ላይ የጉምዝን ሕዝብ የሚዘልፍ ተፈልጎ አይገኝም። የኔ ጽሑፍ “የጉሙዙ ኢነተርሃሙዌ” ነው የሚለው። ኢሕአፓ “የጉሙዝ ሕዝብ” ብሎ ካልተረጎሞው በቀር፤ እና በድረገጹ ላይ እንዳይለጠፍ ካስተላለፈው ትዕዛዝ በስተቀር ኢሕአፓ ከሚያቦካው የውሸት ውንጀላ የተለየ ሌላ ሐረግ በጹሑፌ ፈልጎ አያገኝም። ይህ የምለው ፤ብዙ የዋህ ከፍሎችና መሰሪዎች

የኔን ጽሑፍ ኢሕአፓ እንዳለው እየተተረጎመ አንዳይታይ ነው እራሴን እየተከላከልኩ ያለሁት። በዚህ ተረዱልኝ።

የትችቴን ሐተታ ርዕሰ እንዲህ ይነበበባል፦

"አማራዎች እየተገደሉ ኩላሊታቸው ጉበታቸውና የታፋቸው ሥጋ እየተቆረጠ ተጠብሶ በጉምዞች ሲበላ! ጋዜጠኞች፤ አማራ ወጣቶች፤ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችና ምሁራን ዝምታን ለምን መረጡ? {ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ) 8/24/2015} በሚል ነው;።

ርዕስ ከርዕሱ እንደምታዩት አማራ በነዚህ ክፍሎች የተከዳ ማሕበረሰብ ነው {ለ24 አመት ሙሉ!!!}።የኔ እውነት ነው። አማራ ብየ ስል ከወልቃይት እስከ ሸዋ ያለው፤ጎንደር ወሎ ጎንደር፤ጎጃም ሐረር የትም ደምበር የተበተነው አማራ ማለቴ ነው።

ሕዝቡ በተለይ አማራው ከመላ ኢትዮጵያ በሚኖርበት አካባቢዎች የተከፈተበትን የዘር ጥቃት ዘመቻ፤ እራሱን ከተሰነዘረበት የዘር ማጽዳት ጦርነት ለመከላከል እንዲችል፤ እራሱን ማንቃት እንዳለበት በተባረሩትና በተገደሉት አማራዎች ስም እሮሮየን እና ጥሪዬን በትችት መልክ በማቅረቤ ኢሕአፓ ድረገጹ ተለጥፎ ሲያበቃ እንደገና እንዲነሳ ማድረጉ ለአማራ ቆሜአለሁ የሚለውን ሐረጉን ምን ያህል እውነትነት እንደላው የሚያስገምተው ነው። ተደጋጋሚ የስልክም የቴክሰት መልዕክትም የድረገጹን አዘጋጅ ማብራሪያ ጠይቄ መልስ አላገኘሁም።

ጽሑፌንም ለጥፈው ያነሱትም መሆናቸው አላወቅኩም ነበር፡ አንድ ወዳጄ ነው ደውሎ መነሳቱን የነገረኝ።ለእዛውም በጨዋ ደምብ ጠይቄ መልስ አላገኘሁም። ለጥያቄዬ ማብራሪያ መልስ ግን በድርጅት መግለጫ ተጽፎ ሳነበው እጅግ ገረመኝ፤ አበሳጨኝም።ድርጅቱ የለጠፈው መልስ የማይገባ ነው። ጸያፍ እና ስድብ የተሞላበት መልስ ያውም ጭራሽኑ "ለፈረንጆች

ማስደሰቻ ፍጆታ የቀረበ ዜና ነው ያስተላለፋችሁት” ብሎ መወንጀሉን አስገራሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ድርጅቱ በእዛው አልተመለሰም። “ደርጎች” እያለ ነው የወነጀለን። ደረግ? ማነው ደርግ? ደርግን የሚያውቀው “ከማንኛችንም በላይ ኢሕአፓ ነው” ደርግ ለኢሕአፓ ይቀርበዋል፡፤ እኔ ደርግ ደሞዝ እየከፈለ አላኖረኝም ፤ አላበላኝም፤ ደረግ አሰረን ፤አሰቃየኝ አንድሰደድ አደረገኝ አንጂ፤ የመንግሰቱ ገንዘብ አልተቀበልኩም፤ ዝምባቡዌ ሄጀ ከደርግ መሪ ጋር መነጋገሬን እንደ ኢሕአፓዎች ተወንጅዬ አለውቅም። ወንጃዮችም ተወንጃዮችም ፊት ለፊት ማቅረብ ይቻላል “ፈቃደኞች ከሆኑ፤ ኢሕአፓን በዚህ ጉዳይ የከሰሰን አንደኛው ክፍል ለመቅረብ ዝግጁ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ”። ምንድር ነው ነገሩ? ደርጎች? ማነው ደርግ?

ኢሕአፓ ደርግ እያለ የሚወነጅላቸው ግለሰቦች ካሉ፤ እነሱም በበኩላቸው ኢሕአፓን ምን ብለው አንደሚጠሩትና እንደሚወነጅሉት እራሱ ኢሕአፓ የረሳው ይመስላል። ደርጎች የሚባሉ ሰዎች ካሉ ደርግ ስለ አማራ ወላጆቹም ሆነ ወንድሞቹ እና እህቶቹ በዘር ጥቃት ሲጠቁ የመከላከል፤ የመጮህ፤የመከራከር መብት የለውም ብሎ አንዲወስን “ኢህአፓ” መብቱ ማን ነው የሰጠው? ለመሆኑ ከየት ነው ይህ ድፍረት ሞራል ሊያገኘው የቻለው? ይኼው ለጸረ አማራዎች ለእነ አንዳርጋቸው ጽጌና አመራ ይቅርታ ይጠቅ እያለ “ዛሬ ደግሞ ኢትዮጵያን ፖለቲሺያን” የሚል ሰም ፈረንጆች ሰጠተውት በየደርገጹ እየተለጠፈለት ያለው የአነግ መዝሙር ዘማሪው “በቀለ ገርባ፡ ለተባለው ቂመኛ እና አፍራሽ ሰው ጩሖታችሁ አሰምታችሁ የለ? ደርጎች ስለ አማራ ቤተሰቦቻቸው መጮህ አይችሉም ማለት ምን ማለት ነው?

ደርግ ብሎ እየወነጀላቸው ያሉትን ሰዎች “ወንጀል” ፈጽመውብኛል ብሎ የሚከሳቸው ሰዎች ካሉት እስካሁን ድረስ ማን ይዞት ነው ኢሕአፓ ወደ

ፍርድ ቤት ሄዶ ያልከሰሳቸው? ስድብ መረጃ አይጠይቅም ስለተባለ ነው? ወይስ ስድብ ከፍረድ ቤት መመላለስ ቀላል ስለሆነ?

የአማራ ጥቃት ለማስተጋባት እያስመሰሉ “አማራ ነን ባዮች” በአማራ ስም ሌሎችን ሕዝቦች እየዘለፉ ናቸው፤ እነዚህ ደግሞ “አማራዎች ነን የሚሉ ደርጎች ናቸው” ብሏል። ሕዝብን የሚዘልፉ ግሰቦች አንዳሉ የሚካድ አይደለም። በየፓልቶኩ በዘር ጥራት ሰክረው አረፋቸው በሕዝብ ላይ የሚተፉ ብዙ “ቆሻሻ ሕሊናዎች” አሉ። ሆኖም ሁሉም ‘ድርጎች’ አይደሉም።

ሆኖም ኢሕአፓ በድርጅቱ ውንጀላ መሰረት፤ ሞረሽንም ሆነ ማንም ሰው በመግለጫው ላይ አማራን በመወከል “ሕዝብን” የዘለፈበት ሐረግ ማሳየት አለበት። ካለይ አስቀድሜ በጥቅስ ሞረሽ ስለ ጉሙዝ ነገድ እና አማራ ነገድ የጠቀሰው ከሆነ ኢሕአፓ ከበስተጀርባው የሚያሳክክው ነገር ከሌለ በቀር ለእንዲህ ያለ ድርጅታዊ አቃቂርና ውንጀላ የሚያዘጋጅ ነገር ምንም አልታይ ብሎኛል። ዘረኞች ያላቸው አንዳንድ ሕዝብን የሚዘልፉ፤ ትንንሽ ሕሊና የተሸከሙ ‘ማይሞችን’ ማለቱ ከሆነ አንዳንዶቹም እኔም እራሴ በፓልቶክ ቃለ መጠይቅ ተጋብዤ፤ ቀርቤ አጋልጬአቸዋለሁ፤ ተጋፍጬአቸዋለሁ፤ዝም አንዲሉም በመጠኑ አድረጌአለሁ፤ ለውጥም ታይቷል።

ኢህአፓ ካልታመመ በቀር እኔን በደርግነት አንደማያስቀምጠኝ/እንደማይነጅለኝ ተስፋ አደርጋለሁ? ካሁን በፊት በቀርቡ ከአገር ቤት መጥቶ የአሜሪካን ሃምበርገርና ፒሳ ገምጦ ልቡና ጡንቻው እያበጠ ያስቸገረው፤ “የአገሬን አቀበትና ቁልቁለት ወርዶ ጠመንጃ ተሸክሞ ከገበሬው ጋር ቁጭ ብሎ፤አብሮ ምሽግ ላይ ተኝቶ፤ ተጫውቶ አውርቶ፤ መከራውን ያላዳመጠ ኢትዮጵያን የማያውቃት” አንድ የእነሱ “ጋጠ ወጥ” ወጣት ነኝ ባይ በደርግነት ሲያማኝ አንደነበር

ሰው ነግሮኝ፤ ከመሳቅ ሌላ ምንም አላልኩም። የሚገርመው ደግሞ፤ እኔንም እኮ ማንነቴን አያወቀኝም። እኔ ከአገር ስወጣ ወደ እዚህ ዓለም የመጣ አዲስ የተወለደ አዲስ ምጢጢ እኮ ነው ደግሞ አንዲህ የሚለኝ። አይገርምም?

እንዲህ ያሉ ፍጡራን እኮ ስም በማጥቆር ከወያኔዎችም የማይሻሉ 'ትንንሽ ሰዎች" ናቸው። በመበሳጨቴ ይቅርታ አድርጉልኝ። እኔ እራሴ ሳስበው፤ አማራን ነፍጠኛ እያሉ እንደ ኦነግ፤ ወያኔና ሻዕቢያ ዛሬ ደግሞ ግንቦት 7 መሳሰሉ በአማራው ላይ ቆሻሻ አፋቸውን የሚጸዳዱት አዲሶቹ የሻዕቢያ አሽከሮች የሆኑት የግንቦት 7ቱ እንደ እነ "ኤፍሬም ማዴቦ" የመሳሰሉ ማፈሪያዎች፤ ስለ እሚነዙት የአማራ ጥላቻቸው እንታገል ወይስ ከወያኔ? ከስንቱ ጋር ልግጠም? አሁን ደግሞ ኢሕአፓ? ነውር ነው። ይኼ በጣም ይከብዳል።

ዝም እንዳንል፤ ሊሂቃን እየተንሸራተቱ ውድቀታቸው እንደ አህያ ሲደጋግሙት እንዴት ዝም እንበል? በነዚህ ልሂቃን ሰንፍና ምክንያት አማራውን ሜዳ ላይ "ለሰው ጅብ" ጥለውት ስለ ዲሞክራሲ ሲተርቱና ሲዘምሩ በማየቴ ጀምሬ ያቆምኳቸውን ሁለት መጽሐፍቶች ሳልጨርሳቸው በእንጥልጥል አሉ።

እውነት እላችኋለሁ፤ ጌታቸው ረዳን ለቀቅ ብታደርጉት ጨዋነት ነው ። ትግሬዎች ሲመስሉ አንዲህ ይላሉ፤ **"ኣብ ዝሑል ጸባ ዚለመደ ሃንቀላስ ኣብ ውዑይ ጸባ ኣትዩ ሞተ"** የአማርኛ ትርጉሙም፤ {ቀዝቃዛ ወተት ውስጥ መምቦጫረቅ የለመደ ዝምብ፤ እሞቀ ወተት ውስጥ ገብቶ ሞተ} ማለት ነው።

እስኪ ከድርጅቱ መግለጫ አንዳንድ ላሳያችሁ እና ልደምድም፡ የድርጅቱ መግለጫ ፤እንዲህ ይላል ርዕሱ፤-

## ከፍኖተ ዴሞክራሲ
## በ አማራ ሕዝብ ስም ሌሎችን መዝለፍ የሚወገዝ ነው

የውሸት ጋጋታው እንዲህ ሲል ይጀምራል።

"ይህን አቅዋም ማስተጋባቱ የግድ የሆነብን አማራው ህዝብ ተበደለ በሚል ጸያፍ ዘመቻዎች በሌሎች ህዝባችን ላይ መካሄዱ ስለቀጠለ ነው "

ኢሕአፓ፤ ይህንን በማስረጃ አስደግፎ፤ ማን እና በማን ሕዝብ፤ "ሕዝባችን" ብሎ የሚጠራቸው "ሌሎች ሕዝቦቹ" ኢሕአፓ እነ ማን መሆናቸው በግልጽ ስም እየጠቀሰ ካላቀረበ "ውሸታም ነው" ድፍን ያለ መግለጫ እና ውንጀላ ማንን ነው እየወነጀላችሁ ያላችሁት የሚል ጠያቂ ይመጣል፤ ስለዚህ ግልጽ አድርጉት።

"ዝምታ ሕዝብን ለጥቃት አሳልፎ መስጠት በመሆኑ ግዳጅና ሀላፊነትን መካድ ይሆንብናል ።"

ግዳጃችሁ ምንድ ነው? ሐላፊነታችሁስ ምንድ ነው? ሐላፊነት ማለት ምን ማለት ነው? ማነው ሕዝብ ሲያጠቃ እና ሲያስጠቃ በታሪክ የሚከሰስ? ዝምታን የመረጠ? ማን በማን ላይ ነበር ማነው ዝምታን ያሳየ? ከኔ እና ከሞረሽ ሌላ በዚህ ነገር አንስቶ የጻፈ/እሪ፡ያለ ጥሪ ያቀረበ ሰው ሰሞኑ የለም። ስለዚህም ክሳችሁ በኔ እና በሞረሽ ላይ ነው። ስለሆነም ነው ጽሑፌን ከድረገጻችሁ ያነሳችሁት በመግለጫችሁ መሰረት፤ "ሕዝብን ለማጥቃት" የተነሳ ግለሰብ ወይንም ቡድን ካለ ግለጹ፤ ካልሆነ ሕዝብን ለጥቃት አሳልፍን አንሰጥም ብላችሁ "በላዩ ላይ ለመዝምት የተነሳችሁበት ክፍል" ከኔ እና ከሞረሽ ሌላ ስለሌለ፤ ራሳችሁን ማረም ይኖርባችኋል?

“በሰሞኑ አማራው ህዝብ ከቤኒ ሻንጉል ተፈናቀለ በሚል ለዚህ ዋናውን ተጠያቂ ወያኔን በማውገዝ ፈንታ በጉምዝ ሕዝብ ላይ የተከፈተው ጸያፍ ዘመቻ የአማራን ሕዝብ ተገን አድርጎ በመሆኑ ሊወገዝ የሚገባው ነው።”

ይህ አሁን በድርጅት ስም መውጣት የነበረበት ነው? ከተራ አሉባልታ የማይሻል? ወያኔን ሳናወግዝ፤ በጉምዝ ሕዝብ ላይ የዘመትኩበትን ጽሑፌን አንዲት ሐረግ እንደ ማስረጃ ማቅረብ ትችላለችሁ? ይህ ውሸት ካላረጋገጣችሁት፤ ሕዝብ ፊት ተዋርዳችኋል። በዚህ ምክንያት ነው ጹሑፌን ከድረገጻችሁ ያስነሳችሁት?

አማራውን ከአካባቢው ለማስወጣት ተደጋጋሚ ማባረሮች ተደርጓል፡ አማራው ሙሉ በሙሉ አልለቅ ሲላቸው አማራው ደንግጦ እንዲወጣ ለማድረግ **“አርደው በልተውት…** ይህ ያደረጉ ደግሞ **የጉሞዝ ብሄረሰብ** ይሁኑ እንጂ **እስላሞች** ናቸው።” ሲል መስካሪው በቃለ መጠይቁ ጉሙዝ ብሄረሰብ አማራውን ብሐረሰብ አርዶ መብላቱን ተናግረዋል። {ቃል በቃል ነው የምስክሩ ቃል ከላይ የጠቀስኩት}

ይህ መሰረት በማድረግ ሞረሽ “ የጉሙዝ ጎሳ አማራውን ነገድ አርዶ በላ” ቢል መስካሪው ከተናገረው ሌላ ምን ልዩነት አለውና ነው “ሞረሽ የጉምዝን ሕዝብ ዘልፏልና ይቅርታ ይጠይቅ” ብሎ ኢሕአፓ በማይቦካ ነገር ገብቶ ሞረሽን ከጉሙዝ ሕዝብ ለማናከስ የሚያቦካው? ለምንድ ጥቅም ነው? ድርጅቱ ተቀባይነት አጥቶ አማራው ያለ ምንም ዘጋቢና ጧሂ እንዲቀር ለማድረግ ነው? ኢሕአፓ ስለ አማራ ዘግቤአለሁ ይላል፡ በዚህ ይዘግባል በማግስቱ ደግሞ መዐድን ሲዘልፍ የነበረውን ነው ዘግቤአለሁ የሚለን? {ለሌላ ቀን እናቆየው}

ፕሮፌሰር መስፍን እንኳ ባቅማቸው፤ ጎንደሬው ከትግሬው እንጂ ከሸዋ መጋባቱ ትንሽ ይቀፈዋል፤አማራ የሚባል የለም። ይላሉ። አማራ ናቸው ተብለው የተገደሉ ሲዘግቡ ቆይተው፤ በማግሰቱ ደግሞ “አማራ የሚባል

በኢትዮጵያ ምድር፤ የለም፤ አማራ አለ እያሉ የሚንጫጩ ፤ እውጭ አገር የሚኖሩ አሉ፤ የነሱ "አማራ የሚባል ማሕበረሰብ አለ" የሚለው "በሽታ" ወደ ኢትዮጵያ እንዳይጋባብን መጸለይ ነው" ብለው ሲሉ በአማራነታቸው ተገደሉ ሲሉ የዘገቡትን ባመግሰቱ አማራ የሚባል የለም ብለው ያፈርሱታል።

የሚገርመው ደግሞ፤ የተገደሉት ዘመዶች እና የተባረሩት ደግሞ "አማራዎች ተለይተን እንድንገደል፤ እንደንባረር፤ገደል አንደንገፈተር ተደርገናል" ብለው ነው፤ፕሮፌሰሩንም ሆኑ አብረዋቸው ለነበሩት ዘጋቢዎቻቸው {ኢሰመጉ}፤ የሚገልጹት። እሳቸው ደግሞ "አማራዎች አይደላችሁም' ብለው አማራዎች ነን ለሚሉት አይደላችሁም ይሏቸዋል። ከመለስ ጋር ያደረጉት ውይት አድምጡ። ታዲያ ሁለት መንገድ ነው እያየነው ያለው። ገምቢ እና አፍራሽ፡ስራ ይሰራሉ" ኢሕአፓም አንደዚያ ነው። ሰው ሰውን በላ የሚል ዜና፤አትዘግቡ፤ አልተደረገም፤ ብሎ ይክዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝችን ከጥቃት እንከላከል ይላል።

በዚህ ዘገባ ኢሕአፓ ሞረሽ ሊዘግበው የሚፈልገው "አማራ በጉሙዝ ብሔረሰብ አስላሞች ተበላ" ብሎ እንዲል ይፈልጋል? ነገዳቸው ጉሙዝ ነው፤ ሃይማኖታቸው እስላሞች ናቸው ተብሏል። እንደ መስካሪው ምስክርነት ቃለ መጠይቅ በተደመጠው መሰረት። ታዲያ ሞረሽ "የጉሙዝ እስላሞች" ባለማለቱ ነው፤ ወይስ ምንድ ነው?

የሚገርመው ደግሞ "ጉሙዞች አማራውን አርደው በሉት" ማለት የሚጠበቀው አፍሪቃን ከሚጠሉ ፈረንጆች እንጂ ከኢትዮጵያዊ መሆን አልነበረበትም ይላል {ፈረንጅ የሰው ስጋም፤ የአይጥም፤ የፈረስም፤ትልም ውሻም ተብልቶ፤ ሰው ገድለው የሰው አንጀት ወደ ሳሙና ሰርተውት አንደማያውቁ ኢሕአፓ ፈረንጆች ጻድቃን ሊያደርጋቸው

ይፈልጋል!!!ፈረንጅ በምን ግብረ ገብ እና ሞራሉ ነው አፍሪካን የሚመጻደቅበት?} ።

የሚገርመው ኢሕአፓ {1} **ጉሙዞች** አማራን ገድለው በሉት "አትበሉ" ዘረኝነት ነው፤ ስድብ ነው ይለናል፤ {2} **የጉሙዝ ብሔረሰብ** አማራውን ነገድ አርደው በሉት አትበሉ ይለናል። ሁለቱንም አትበሉ ይለናል። እንዴት መቅረብ ነበረበት ተብሎ ሲጠየቅ ደግሞ ፤" **ሕዝባችን የትም ቢሆን የት ሰው አይበላም ፡ ይህን ውሸት ማሰራጨት ኢትዮጵያ ላይ መዝመት ነው"** ሲል በጸረ ኢትዮጵያ ይከሰናል። ሰው አልተበላም፤ ይህ ውሸት ነው፡ በማለት እኛን ብቻ ሳይሆን እዛው ያሉት ምስክሮችንም የውሸት አፍላቂዎች አድርጎ እኛንም የውሸት አሰራጮች በማለት "ውሸታሞች" ብሎ የዘልፈናል።

ኢሕአፓ እዛው እቦታው ድረስ ሄዶ እውነቱን እንዲዘግብልን እና ሰዎቹን ለምን ትዋሻላችሁ ብሎ ከምስክሮቹ ጋር ይጋፈጥ። አድራሻ የለኝም የሚል ከሆነም "ዋሾች የተባሉት ምስክሮችም ሆነ አሰራጪዎች በሚፈልጉት ራዲዮን ጠርተው ይከራከሯቸው። ሕዝብቻን የትም ይሁን የትም ሰው አይበላም የሚለውን የኢሕአፓ ክርክሩ ከወደታች በመረጃ ኢትዮጵያ ምድር ውስጥ ከጥንት ጀምሮ ይደረግ እንደነበረ በማስረጃ አቀርባለሁ። ልብ እንድትሉ "ሕዝብ" እያለ ያለው እራሱ ኢሕአፓ እንጂ ማንም ሰው "ሕዝብ" ብሎ የጻፈ የተናገረ የለም። ሕዝብ በብዙ መንገድ መተርጎም ሰለሚቻል የኛ እና የኢሕአፓ የሕዝብ ትርጉም ይለያያል። ጀርመኖች የአይሁዶችን አንጀት ወደ ሳሙና ለውጠውት ነበር" ተብሎ ሲጻፍ "የጀርምን ሕዝብ" ማለት እንዳልሆነና አድራጊዎቹ ግን "የጀርመን ነገዶች" መሆናቸው ግልጽ ነው። ኢትዮጵያዊያን እውነተኞችና የዋሃን ናቸው ሲባል፤ ሁሉንም አያጠቃልልም። ኩፉም፤ዋሾም ነብሰገዳይም፤ጨካኝም፤ አምታቺ፤ቀውሰኛ፤አታላይ የለበትም ማለት አይደለም። አነጋገር ዘይቤዎች እንደተርጓሚው ነው። ኢትዮጵያዊያን ሯጮች ናቸው ሲባል፤ 90 ሚሊዮን ሰው ሯጭ ነው ማለት አይደለም። እንኳን ማራቶን ላይ ሊሮጥ፤ ከጠላ ቤት ወደ ጠላቤት እያነከሰ መራመድ ያቃተው እንደቆረቆንዳ በሞጃሌ

የተገረፈ ባለ እግር ብዙ ነው። "የአማራ ነገድ በጉሙዝ ጎሳ ታርዶ ተበላ" ሲባልም፤ የጉምዝ ሕዝብ አንዳለ አያጠቃልልም። አንዴት ነው ነገሩ?

ኢሕአፓ ውሸቱን በቅቤ ለመወልወል ሲያሻው አንዲህ ይላል፡ **"ሀይማኖት የላቸውም፤ ስለዚህም ሰው የሚበሉ አረመኔዎች ናቸው፤ ብሎ ልፈፋም አማራ ነን ባዮቹ፤ ምንኛ ኋላ ቀርና የሀገርን ስምና የአንድነት መሰረት አውዳሚ እንደሆኑ ያሳያል።"** ይላል። አማራ ነን ባዮቹ ማለት ምን ማለት ነው? በሚገባ ሞረሽ ውስጥ ያሉ አማራዎች ነን ብቻ ሳይሆኑ "አማራዎች" ናቸው። እንደ በረከት ስሞንና ሕላዌ ዮሴፍ "አማራዎች ነን ባዮች" የሚባልላቸው አይደሉም። አማራዎች ናቸው። ምንድር ነው ነገሩ?

መስካሪዎቹ እየነገሩን ያሉት "ጉዳዩን የፈጸሙት ሃይማኖታቸው እስላሞች" "ነገዳቸው ጉሙዝ ብሄረሰብ" ብለው ነው ነገዳቸውና ሃይማኖታቸውን እየነገሩን ያሉት። ኢሕአፓ ደግሞ ከምን እንዳመጣው አላውቅም፤ ይህን የፈጸሙ ""ሀይማኖት የላቸውም፤ ስለዚህም ሰው የሚበሉ አረመኔዎች ናቸው" ብለው የሚለፍፍት ኋላ ቀር የሆኑ የአገር ሰም እና መሰረት አውዳሚ የሆኑ "አማራ ነን" ባዮች ...." በማለት ነው እየከሰሰ ያለው። የሰው ስጋ በልተዋል ተብለው እየተወነጀሉ ያሉት "ኢሕአፓ" እንደሚለው "ሃይማኖተ ቢስ ፤አረመኔዎች ሳይሆኑ "ሃይማኖት ያላቸው አረመኔዎች ያልሆኑ እስላሞች ናቸው"'። ምንድር ነው ነገሩ?

ታዲያ አረመኔ ብቻ ነው ይህ ድርጊት የሚፈጽም ብሎ ኢሕአፓን "ሹክ" ያለው ማነው? በበደኖ አርባ ጉጉ ጉደኛ ወንጀል የፈጸሙ እስላሞች የሉበትም ሊለን ነው? የሚገርመው ደግሞ፤ ኢሕአፓ "ወያኔ ነው እንጂ ሌላ ማንም ፈጻሚ ወንጀል የለም" ሲል አነግን፤ ሻዕቢያን የመሳሰሉ ጸረ አማራ ሃይሎችን አማራን አጥፋ እያሉ የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈጸሙ የአማራውን አገር ካርታ ወደ እራሳቸው ያጠቃለሉ፤ አውጭ አገር ተሰድደው እጎናቸው ተቀምጠው እያሉ፤እያዩዋቸው፤ ዘረኞቹ ራዲዮን ከፍተው፤አልጀዚራ ቲቪ ድረስ እየቆላወጡ፤ ዛሬም አማራ ይቅርታ ይጠይቅ እያሉ የሚጠይቁ ወያኔ ያልሆኑ ጸረ ወያኔ የሆኑ፤ አማራን ለማጥፋት አገሩን ዘሩን ሰንደቃላማውን ለማጥፋት ፕሮፓጋንዳ የሚዘረጉ

“የቆዩ እና አዳዲስ ወጣት ዘረኛ ኢንተርሃሙዌዎችን” ወንጀል የሰሩ እና ተጠያቂዎቹ በነፃ ለመልቀቅ ወያኔ እንጂ ሌላ ወንጀለኛ የለም ይለናል።

ይህ ከንቱ መመጻደቅ፤ በወያኔ ብቻ ማትኮር ‘ሕዝብን እየበከለ ያለው፤ ተበላሽቶ የሚገኘው የሕዝባችን ባሕል፤ መካድ ነው። ለሕዝቡ የባሕል ለውጥ ወያኔ ብቻ አይደለም ተከሳሹ።ግንቦት 7 እንደሚለው ክርክር እኮ ነው ኢሕአፓ የሚተርከው ትረካ። ወያኔ እንጂ ሌላ ጠላት ኢትዮጵያ የላትም፡ ይላሉ። ስለዚህ ወያኔ ከጣልን አገረ ነገሩ ሰላም ይሆናል፤ የሚል ቧልትና የልጆች ንግግር፤ ጥልቀት የሌለው ሰርጾ የማይወጋ፤ ላይ ከላይ የሚንሸራተት የበረዶ ንጣሪ ፖለቲካ ነው።

ወያኔ ለማሕበራዊም ሆነ ለፖለቲካው እንዲሁም ባሕለዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ለውጥ ብቻውን ተጠያቂ አይደለም። ከኢሕፓ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያሉት ሊሂቃን እና ድርጅቶች ለማሕበራዊ ቀውስና ያስተሳሰብ ለውጥ ተጠያቂዎች ናቸው። 40 አመት የባሕል ለውጥ፤ ያስተሳሰብ ለውጥ፤የህሊና አጣባ፤ ተፈጽሞበታል። ለዚም ነው አንዳንዶቻችሁ “ይቅርታ ጠይቀናል” ስትሉ የምትደመጡት። ይቅርታ የጠየቃችሁበት ሁኔታዎች፤ በሕዝቡ አስተሳሰብ፤ አኗኗር፤ብስለት ፤ ፖለቲካ፤ሃይሞታዊ፤ባሕላዊና ጭካኔአዊ የሞራልና የድስፒሊን ለውጦች በሕዘቡ ላይ ሲጫንበት ወያኔ ብቻውን ተጠያቂ ማድረግ “ይቅርታ ጠይቀንበታል” ወዘተ...ወዘተ....የምትሉበትን አስተዋጽኦ አላደረግንም እና ይቅርታውን ስበነዋል የምትሉ ከሆነ ሌላ ነገር ነው። ወያኔ ብቻ ነው “ሽብርተኛ፤ወያኔ ብቻ ነው ኮሚኒስት፤ ዘረኛ.....ሰው ገዳይ.////ጸረ ኢትዮጵያ..ወያኔ ብቻ ነው ኢትየጵያን ለማፍረስ የተነሳ..” ብሎ ለወያኔ ብቻ መወንጀል፤ እየተደረገ ያለው የወንጀል ስራ ተባባሪዎች፤ከወየኔ የተለዩ ተዋናዮች፤የውጭ አገር ተቀጣሪዎች...ባንዳዎች የሚሰሩት ወንጀል እንዳይጋለጥ መተባበር ነው።

አማራው ሲገደል፤ አማራው ስጋው ሲበላ፤ “ለውጭ አገር ለፈረንጆች ፍጆታ እንዳይውል፤ ዝም በሉ፤ አፋችሁን ከደኑ” እየተባለ ኣማራ ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃት ዓለም እንዳይሰማው፤ ሕዝብ እንዳያውቀው

እየተደረገ ለዚህ ጥቃት ተዳርጃ ል። ተጠያቂው ወያኔ ብቻ ሳይሆን “ዝም በሉ፤ሰው እንዳይሰማ፤ ባሕላችን አይደለም፤እንዳንሰደብ” የሚሉትም ጭምር በጨዋታው ገብተውዋል እና ተጠያቂዎች ናቸው።እኛ አንዳንሰደብ አማረው እየተገደለ ስጋው በሰው ጅቦች ይበላ
ማለት “ግደ ቢስነት ነው።

ለአማራው መጠቃትም አንዲህ ያለ “ድፈን፤ድፍን፤ከደነው ክደነው„ጨዋታ ነው አማራውን ለጥቃት ያበቃው። ፡አንድ ሕዝብ ነን፤ ተዋለደናል፤ እባካችሁ ዝም በሉ.....በዛው ያሳልፈው፤ ሁሉም አይደለም አንዳንድ ባለጌዎች የፈጸሙት ነው እና ህዝብን አናቃቅር...እየተባለ አጉል ፖለቲካ እና ሽምግልና ተገብቶ “አማራው ይሙት፤ይጥፋ” የሚሉ ጥልቀት የሌላቸወደ ደነዞን ብቻየን ቆሜ ለብዙ አመት የምዋጋውም ለዚህ ነው። እነዚህ አንድ ሕዝብ ነን ፤ተዋልደናል እና ዝም በሉ የሚሉ፤ “እጨዋታው ውስጥ የገቡ የኢንተርሃሙዌው አጫፋሪና አቃጣሪዎች ናቸው”እንዲህ የሚሉት። እነዚህ ደግሞ ለማንም የማይበጁ ፡ሚዲዮከር” “ውሃ አቀባይ፤ አረግራጊ” ነው።

ድንገት ባንድ ፓልቶክ ክፍል ገብቼ የሰማሁትን ልንገራችሁ። አንድ የኢሕአፓ አባል ነኝ የሚል የኔን ስም እየጠቀሰ ሲምቦጫረቅ የሰማ አንድ አድማጭ እንዲህ ይለዋል።
“አውነት እናንት ኢሕአፓዎች አሁን የምትሉት ነገር መርምራችሁት ነው? እኔ ወያኔ ከመግባቱ በፊት የድርጅቱ የኢሕአፓ አባል ነበርኩ፡ አንተ ብቻ አባል ሆነህ የነበርክ አይምሰልህ፡ ኢሕአፓን በደምብ አውቀዋለሁ፤ ምን አንደሰራ አውቀዋለሁ። ጌታቸው ረዳ ጻፈው ስለምትለው አንስተህ አውግዘሃል፡ ለመሆኑ፤ አንድ ታሪክ ልንገርህ ፡ኢትዮጵያ ውስጥ እያለሁ የተፈፀመው፤ በማለት አንዲህ ይላል፤

“በምስራቁ ኢትዮጵያ አካባቢ አንድ የአሰመጉ መርማሪ/ኢቨስቲገተር እቦታው ድረስ ሄዶ ያየውን ልንገርህ። አንዲት አማራ የሆነች እርጉዝ እናት የነበረች ሆዷ በቢላዋ ተቀድዶ፤ ሽሉን አውጥተው፤ ገዳዮቿ ጡቷን በቢላዋ ቆርጠው ከጡቷ ስጋ ሲቀምሱ በዓይኑ አይቶ ፎቶግራፍ እንኳ ለማንሳት

ተሳቅቆ ባዶ እጁን ተመለሰ። ለምን ፎቶግራፍ አንኳ አላነሳህም ተብሎ ሲጠየቅ፤ ከባሕላችን ውጭ የጭካኔ ድርጊት ስለሆነ ባሕላችንን ማስሰደብ ይሆናል ብየ ነው;; በሚል አላነሳሁትም።" ሲል የተደረገው ክራይም/ወንጀል የዓለም ሕዝብ በዓይኑ አይቶ፤ሰምቶ የነገሩ አሳሳቢነትና ጥልቀት ምን ያህል መሆኑን አንዳይገነዘብ፤ ሳይውቀው መርማሪውም ወንጀሉን ደብቆታል።" ሲል ይሞግተዋል። እኔም የዚህ ወንድም በሳል አገላለጽ በጥሞባ አድምጬ ተመስጬ በልቤ አስተዋይነቱን አመሰገንኩት።ኢሕአፓው ተከራካሪው ሰውዬ ግን "ባሕላችን አይደለም" "ፈረንጅ ይሰድበናል" እያለ ከንቱ ንትርክ ሲገባ ሰምቼ ገርሞኛል። ኢሕአፓ ድረጅትም የሚለው "ይህንኑ ድንቁርና ነው" በመገለጫው የለጠፈው።

ሌለቹን ሐተታዎቹን "አስፈላጊ ከሆነ" በሌላ ቀን አምለስበታለሁ፤ለዛሬ ግን ሕዝባቻን እንዲህ አድርጎ አያውቅም ፤ተሰምቶ ተደርጎ አይታወቅም፤ የሞረሽ፤አማራ ነን የሚሉ የትምክህተኞች ኋላ ቀር፤ አገር አፍራሾች ወይንም የፈረንጅ ውሸት ፀሐፊዎች ብቻ አንጂ አገርኛ ጸሐፊዎች እንዲህ ሰጽፉ አይታወቅም.....ወዘተ እያለ ያለው ኢሕአፓ ትንሽ መረጃ ከጥንት ኢትዮጵያዊያን ጸሐፊዎች ምስክርነት በሊቃውንት የተጠቀሰውን ሰው በሰው በምድራችን ተብልቶ አንደሚታወቅ መረጃ ልስጥ እና ልደምድም፤-

"በከብት ማለቅ የተነሳ (በሐረር ሕዝብ ላይ) ችጋር ጠናባቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ገራድ እስላም ተሸመ፡፡ ኖሌ ላይ ብዙ ሰው በችጋር አለቀበት፡፡ ውሃም ቀጅ አልቀረ፡፡ ስለ ረሃቡ ፅናት አንድ ሴት ሰው አርዳ በላች፡፡ አንድ ሰው ነበረ በሐረር በየቀኑ ድሀ ይፈልግ ነበረ እያረደ ሊበላው፡፡ ረሃብ ስለመጥናቱ በአንድ ቀን ከሶስት ሰዎች ጋር ተቀምጠን የሰው ስጋ እያረደ የሚበላው ሰውየ መጥቶ ከደጃፍ ላይ ስጋውን በሸማው ቋጥሮ ቆመ፡፡ ›ስጋ ግዙ የፍየል ስጋ ነው› አለ፡፡ ከኛ ማህል አንዱ ሰው ›ይህ ነገር የሰው ስጋ መሰለኝ; ብሎ ጠረጠረ፤ ጠየቀውም፡፡ ቢጠይቀው ›አዎን› አለ፡፡ ከዚህ በኋላ ብዙ ሰው አለቀሰ፡፡››

‘Yeharer Tarik’ By: Unknown writer as Quoted by Getachew Haile

***

በዚያን ዘመን ደግሞ በሸዋ እንሳሮ ከሚባል አገር አንዲት ሴት ሰባት ልጆች በልታ ተይዛ ከአፄ ምኒልክ አደባባይ መጣች ንጉሱም እንጦጦ ከእልፍኙ ደጃፍ ተቀምጦ መረመራት እርሷም ‹አዎን ቢርበኝ በላኋቸው› አለች፡፡ እርሷ ግን እንኳን ሰባት ሰው የበላች ቅናሽ ስጋ የቀመሰች አትመስልም ነበር፡፡ አንጀቱዋ ከጀርባዋ ተለጥቆ እጇን እግሯን ማዳት ወርሷት ትንሽ ደኮ ለትባ ታሳዝን ነበር፡፡ ንጉሱም ‹እንዴት አገሬ ጠፋ፣ ደኸየ፤ ዘመዴ አለቀ› ብሎ አዘነ፡፡ እንያም ይዘው ያመጡት ባላጋሮቹ ‹የርሷን ልጅ ትታ የኛን ልጅ ለይታ ከበላች ፍርድ በቃ ይስጡን፤ መሞት ይገባታል› አሉ፡፡ አፄ ምኒልክም ‹ለኔ ስትሉ ተውልኝ፤ ቢጨንቃት ቢርባት ነው፤ ደግሞ ሌላ ልጅ ካላጣኹ ብላ ነው እንጅ ከባሰባት ልጆቿንም ቢሆን አትተውም ማሩልኝ› ብሎ አሰማራት፡፡ ወዲያው ልብሱን ቀለቤዋን ዳርጎ እርሷን ማድ ቤት፤ ልጇን ተማሪ ቤት አገባቸው፡፡

‘Yegojam Tarik’ By: Alqa Tekleyesus Wakijira

***

‹አንዲት ልጅ ወዛ ብላለች ጋይንቲ ደስታ የሚባል ሰው ነበርና እሱ እየረዳት ተነስታ ፍል ውሃ ወረደች፡፡ ብዙ ሰው የተቀመጠው እዚያ ነው፡፡ ይህ ስደተኛው ሁሉ ተቀበለና እዚያ አረደና በላት፡፡ ልጆቻቸውን ጥቃቅኖቹን እያረዱ የበሉ ብዙ ናቸው፡፡››

‘Metshafe Tizita ze Aleqa Lema Hailu‘ By: Mengistu Lema

በውጭ ጸሐፍት የተሰነዱ ሌላ መረጃ ካስፈለገም

"cannibalism" among the Me'en of southwestern Ethiopia” የሚለወን ፈልገው ያንብቡ።

በአጼ ዮሐንስ ዘመን ትግራይ ውስጥ ከፉ ረሃብ ተከስቶ፤  ዓድዋ ከተማ ውስጥም ርሃብ ጠንቶ ሰው አርዶ የበላ ሰው አንደነበር አን ንጉሱ አስጠርተው በአደባባይ አንዲሰቀል ፍርድ አንደሰጡት ካሁን በፊት ሰፊ ሐተታ ጽፌአለሁ፤እሱንም ይመልከቱት።

አማራው ሲገደል፤ሲባረር ዘም የሚሉ ምሁራን፤የፖለቲካ ድርጅቶች ፤ ጋዜጠኞች፤ ታዋቂ ሰዎች “ዲሞክራሲ/አንዳርጋቸው/የፍረ ወይኒ ቡና ይጣፍጣል...ኢሳያስ አፈወርቂ አዳኛችን አጋራችን//////ወዘተ ወዘተ....” ምናመን የሚሉ ቃለ አጋኖ ጸሐፊዎች ፤ የልጅ ጨዋታቸውን አቁመው፤ በአማራ ላይ እየደረሰ ያለወው ጥቃት አንዲመከቱ  ዝምታቸውን፤ ቸልተኛነታቸውና ፌዛቸውን ገታ ያድርጉ እና ፤ አማራውን ከጥቃት ለመከላከል፤ አንዲያመች፤ ሰላማዊ ሰልፍ በተባበሩት መንግስታት ይደርግ፤ ክስ ይመስረት።

በዚህ አጋጣሚ “ሸንጎ” የተባለው ድርጅት በአማራ ለይ የደረሰው በደል ማውገዙና የአማራውን ሰቆቃ ለማጋለጥ መግለጫ መስጠቱ በጣም ያስመሰግነዋል፤ አመሰግነዋለሁ። በርታ መባል አለበት። ሌሎችም እንዲሁ ይከተሉት። ‘ሰው ሰው’ በላ አንጂ ‘ውሻ ሰው ነከሰ’ ብሎ የሚዘግብ ጋዜጠኛ እራሱን መፈተሽ አለበት። ሰሞኑን የተለያዩ ደብዳቤዎችና ስልክ ጥሪዎች በማድረግ ላበረታታችሁኝ ወገኖች አመሰግናለሁ።

አመሰግናለሁ፡፤

ጌታቸው ረዳ (Editor Ethiopian Semay) getachre@aol.com